የልቤ መዝገብ

የልቤን ግድብ ሸርሸሮት ...
አጥር ካቡን ተሻግሮ፤
ከላይ ከሰማያት ፈልቆ ...
ቁልቁል እንደ ንስር በሮ።
ነፍሴን ከውስጤ መንጥቆ ...
ወሰደው ቀልቤን በጉልበቱ፤
ፍቅር የሚባለው ጀግና ...
የማይበገር ክንደ ብርቱ።

ከዘመናት በፊት ያለ ...
ከጊዜ ቀመር ያለፈ፤
በእውቅ የታሪክ ድርሳናት ...
ከጥንት ከጠዋት የተጻፈ።
የልቤን ማህደር ከፈተና ...
ታሪኩን ይከትበው ጀመረ፤
ምንም ያልተጻፈበት ብራና...
ልቤ ሌጣ ስለነበረ።

ፍቅር ከትቦ ያኖረውን ...
ከንጹሁ የልቤ ሰሌዳ፤
አንቢቢልኝ ብዬ ሰጠኻት
ላለችው ከሃሳቤ ጋዳ ።
አነበበች ሁለት ሶስቴ ...
የልቤን ማህደር አገላብጣ፤
ከልቤ መዝገብ ባገኘችው...
በራስዋ ታሪክ ተመስጣ።

እንባሽ

ከአይንሽ ምንጭ የፈለቀ ....
ከተሰበረ ልብሽ የተቀዳ
የቅንድበሽን ግድብ ደርምሶ ....
በጉንጭሽ ቦይ የተነዳ
ያ ትኩስ እንባሽን....
ላኑረው በጽዋ ቀድቼ
በምን ምክንያት እንደተነባ...
ምስጢሩን እንድጽፍ ፈትቼ

ጠብ አርጌ ከመዳፌ
ከጽዋው ቆንጥሬ ወሰድኩና....
አስተውዬ ባየው እንባሽን
ገረመኝ የፍቅር ሆነና...
እንደገና ብዥ ብሎ
የሃዘን ሆነብኝ ድንግት....
መስሎም ታየኝ ባጋጣሚ
ኩልል ያደረግሽው ለናፍቆት....

የደስታም ይመስላል ትኩስ እንባሽ...
አስተውዬ ባየው ከስሩ
ተዘባረቀብኝ ምክንያቱ....
የ እንባሽ መፍለቂያ ምስጢሩ
አባክሽ አስረጂኝ እህቴ
ለምን እንባሽ እንደፈለቀ....
አእምሮዬም መርምሮ አቃተው
ልቤም ለመፍታት ተጨነቀ.....

Back to Meskot

***The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by** Meskot**. You may contact** Tesfaye Hailu Bekele **for comments at** tesfuhay@ethionet.et*